# የዲፕሎማቱ ምላሽ ለኤምባሲው መግለጫ (1)

(ከዘነበ ኃ/ማርያም ገነሜ)

በ"ethiomedia" ቀደም ሲል በተከታታይ ያስነበብኳችሁን እውነተኛ ታሪክ አስመልክቶ ሰነዓ (የመን) የሚገኘው ኤምባሲ በኢትዮጵያ አቆጣጠር ሐምሌ 29 ቀን 2001 ዓ.ም (እ.አ.አ ኦገስት 5 ቀን 2009) የሌሎችን ባለሙያዎች የትኩረት አቅጣጫ እንዳያስት ለማስገንዘብ በሚል "ጋዜጣዊ መግለጫ" ማውጣቱ ይታወሳል:: አረቦች "ትርጉም የሌለው ሳቅ የህመም ምልክት ነው" እንዲሉ መግለጫው በአጭር አገላለጽ ትርጉም የለሽና ኤምባሲው *እጅህ ከምን?* እንዳይባል ያቀረበው ነው:: ለማንኛውም ግን የትግራዩ አንጃ *...የሌሎችን ባለሙያዎችንና ግለሰቦች የትኩረት አቅጣጫ እንዳያስት...* ማለቱ በእነዚህ አካላት ላይ ያለውን ጥርጣሬ ለማመላከት ነው:: ገዢው አንጃ እንኳን ሌላ አይደለም እራሱንም አያምንም ስለዚህ ይህን ማለቱ ሊደንቀን አይገባም:: በመሆኑም ዜጎችን በሰበብ በአስባቡ ሊያጠቃና ሊያዋርድ የሚያደባን ስርዓት መተማመን ባለሙያውም ሆነ ሌላው ዝምታን መምረጥ የለበትም::

"በጋዜጣዊ መግለጫው" የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን የቅጥር ሁኔታ አስመልክቶ ሠራተኞች ወደ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚቀጠሩት "በችሎታቸው" ነው ይላል:: በእርግጥ እኔና ጥቂት በጣት የምንቆጠር ባለሙያዎች ባለን ብቃትና የትምህርት ደረጃ ወደ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ተቀላቅለን ነበር:: በርካቶች ለወያኔ ካድሬዎች ቦታ መልቀቅ ስላለባቸው ተባርረዋል:: በምትካቸው ከ200 በላይ የትግራዩ አንጃ ተዛማጆችና ተለጣፊዎች ወደ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ገብተዋል:: የተቀረነውን ባለሙያዎች ቁም ስቅላችንን ብታበሉንም ከዛሬ ነገ የተሻለ ይሆናል በሚል የሙጥኝ ብለን ብንቀመጥም በመጨረሻ ለምንወዳት አገራችን እንኳን እንዳንበቃ ማባረራችሁና ዓይናችሁን ለአፈር ማለታችሁ ገሀድ የወጣ የአደባባይ ሚስጥር ነው::

እንደ ውስጥ አዋቂ እኔ ልናገርና በውጭ ጉዳይና በኤምባሲዎች ስንቶች መሀይም ካድሬዎች ናቸው የባለሙያዎችና የባለ ዲግሪዎች አለቃ ተብለው ሹመት ያላቸው? ነገሬን በምሳሌ ላስደግፍና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን ብንወስድ ሚኒስትር ስዩም መስፍን የዩኒቨርስቲ ደጅ ረግጦ አያውቅም፤ ነገር ግን የዶ/ር ተቀዳ አለሙ እና የሌሎች አለቃ ነው:: ኤምባሲውስ ቢሆን፣ እረ ለመሆኑ ማን ነው በችሎታውና በብቃቱ በኤምባሲው እየሰራ ያለው? ቀደም ሲል እኮ የእያንዳንዱን የዲፕሎማትነት ደረጃ የተሰጣቸውን የአቦጊዳ ሽፍቶች ዝርዝርና ማንነት ስለገለጽኩ ራሴን መድገም አያስፈልገኝም::

ኤምባሲው የድጋፍ ሰጪ(Local staff) ብሎ ከሚያሰራቸው መካከል ስንቱ ነው ለመሆኑ ፊደል የቆጠረው? መቼም ለእኔ መዋሸት አይቻልም የእያንዳንዳቸውን የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ ብቃትና ማንነት ጠንቅቄ አውቃለሁ:: ስለዚህ "በጋዜጣዊ መግለጫ" የተገለጸው ነጭ ውሸት መስተካከል ስላለበት ሁለት ሰራተኞችን እንደ ምሳሌ ልጥቀስ:: በቅድሚያ ግደይ ሀይሉ የሚባለው የትግራይ ተወላጅ ወያኔ እና ሙሉጌታ ኒኮላ የኦሮሞ ተወላጅን ኢትዮጵያዊ አንድ ዓይነት ስራ ያከናውናሉ:: ተጨማሪ ስራዎች የኦሮሞ ተወላጅ ለሆነው ሙሉጌታ ተሰጥቶታል:: ማንኛውም ዓይነት ተጨማሪ ሥራ ሲመጣ እንዲሰራ የሚደረገው ይህው ግለሰብ ነው:: አልሰራም እንዳይል የከፋ ነገር እንደሚከተል ስለሚያውቅ ሁሉን አሜን ብሎ ተቀብሎ ይኖራል:: የትምህርት ደረጃውን ስንመለከት ከኢትዮጵያ አንጋፋ ዩኒቨርስቲዎች መካከል ከአንዱ ዲፕሎማ ያለውና የበርካታ ዓመታት የማስተማር ልምድ ያለው ሠራተኛ ነው:: በአንጻሩ ግደይ ሀይሉ ያልተማረ (መሀይም) ራሱን ባለስልጣን አድርጎ የሚወስድ የወያኔ ካድሬ ነው:: በጣም የሚያሳዝነው ለሙሉጌታ የሚከፈለው ደሞዝ 324 (የአሜሪካን ዶላር በወር) ሲሆን፣ ላልተማረው ወያኔ ግደይ ሀይሉ 640 (የአሜሪካን ዶላር በወር) ነው:: ታዲያ ይሄ ምን ማለት ይሆን?

ሌላ ምሳሌ ልጥቀስላችሁ ኤምባሲው ሦስት የጥበቃ ሰራተኞች(ዘበኞች) አሉት:: ሁለቱ ወያኔዎች ሲሆኑ አንደኛው ከፈላ ሀ/ሚካዔል ሲባል ሌላኛው ሀዱሽ ሀ/ሚካዔል ይባላል:: ሌላኛው የጉራጌ ተወላጅ ሞላ ታከለ ይባላል:: ሦስቱም አንድ ዓይነት ሥራ እየሰሩ የደሞዝ ልዩነት ግን አላቸው:: ሁለቱ የትግራይ ተወላጅ ወያኔዎች 325 (የአሜሪካን ዶላር) ሲያገኙ በርካታ ዓመታት ያገለገለው ሞላ ታከለ ግን 210 (ዶላር) ይከፈለዋል:: ይህ ልዩነት ምን ማለት ይሆን? በትግራዩ አንጃ አገዛዝ ሌላው ኢትዮጵያዊ በገዛ ሀገሩ አንሶ እንዲኖር መደረጉ የአደባባይ ሚስጥር ነው:: ይህንን እውነት ለምታነቡ ታዲያ ሙሉጌታና ሞላ በሀገራቸው ባይተዋር አልሆኑም ትላላችሁ? ኤምባሲው ሊደብቅ የሞከረው ይህንን በጉያው የሸሸገውን ሀቅ ነው:: የወያኔ ካድሬ የእውነት ልጆች፤ ሌላው ብሔር የእንጀራ ልጆች ናቸው::

"በመግለጫው" *የአስተሳሰብና የአመለካከት ችግር* እንዳለብኝ በተደጋጋሚ ተጠቅሷል:: ነገሩ ግራ የሚያጋባ ቢመስልም ውስጥ አዋቂዎች አባባሉን በደንብ ጠንቅቀን እናውቀዋለን:: "በስራ ግምገማ" ሽፋን አዳዲስ ሀሳቦችን የሚያመነጭ በስራው ትጉህ የሆነና በህዝብ ዘንድ ተወዳጅነትን እያተረፈ የሚመጣን ባለሙያ ያለውን የሥራ ተነሳሽነት ለማኮላሸት ወያኔ የሚጠቀመው የአስተሳሰብና የአመለካከት ችግር፣ የአቅም ማነስ እና የመሳሰሉትን የሶሻሊዝም/ኮሚኒዝም/ የስልጣን ድንበር መጠበቂያ ስልቶችን ነው:: በእነዚህ ሂደቶች ሰራተኞችን በማባረር፣ ከስራ ደረጃ ዝቅ በማድረግና ደሞዝ በመቀነስ ሰራተኛው አንገቱን ደፍቶ እና ተሸማቅቆ እንዲኖር የማድረጊያ ስልት ነው::

ይህውም ሰራተኛው ሀሳቡን በነጻነት እንዳይገልጽ፣ ለመብቱ እንዳይሟገት እና በራሱ እንዳይተማመን እንዲሁም እርስ በርሱ እንዲፈራራ ተደርጓል:: ይህንን ይምታነቡ የውጭ ጉዳይና የኤምባሲ ሠራተኞች ለዚህም ነው በዚህ ዓይነት ሁኔታ ላይ የምትገኙት:: የአስተሳሰብና የአመለካከት ችግር በሚል ከሚደርስባችሁ ውንጀላ ተሸብባችሁ ለሀገራችሁ ኢትዮጵያ አይደለም ለሌላው ዓለም የሚተርፍ እውቀትና ችሎታችሁ ከሚመክን፣ ጽልመት ያጠላባችሁን የጨለማ ስርዓት በማስወገድ ነጻነታችሁን አውጁ::

ከቤንጃሚን ፍራንክሊን ጥቅስ ለመማር *ያለውን ጥቂት ነጻነት ጥቂት ደህንነት ለማግኘት ብሎ የተወ ማህበረሰብ ሁለቱም አይገቡትም እናም ሁለቱንም ያጣል* ("Any Society that would give up a little liberty to gain a little security will deserve neither and lose both." Benjamin Franklin):: እናም ዛሬ ለምናገኛት ጊዜያዊ ጥቅም ብለን በአስተሳሰብና በአመለካከት ችግር ሰበብ አንገታችንን እንድንዳፋ እንዲሁም በተናገርንና በጻፍን ቁጥር እየተሳቀቅን መኖራችን የማታ ማታ እኛ ብቻ አዋቂ በሚሉት የወያኔ ካድሬዎች ተውጠን እንቀራለን:: ይህ ደግሞ ለሀገርም ለህዝብም ሳንሆን ከንቱ ሆነን እንቀራለን::

ኤምባሲው የአስተሳሰብና የአመከካከት ችግር እንዳለብኝ ገልፆ *...ማንም አገሩንና መንግሥትን የሚወድ ኢትዮጵያዊ የሚረዳው ቁም ነገር ነው::* ብሎ ይደመድማል:: እዚህ ላይ ያለው ትልቁ ተቃርኖ/paradox/ ሀገሩን የሚወድ ማንም ኢትዮጵያዊ ይህንን የትግራዩን ክፉና ጨቋኝ የአንጃ አገዛዝ በፍፁም ሊወድ አይችልም:: አንጃውን/ወያኔን/ እወዳለሁ የሚል ካለም አንደኛ ራሱ ወያኔ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በትርፍራፊው ላይ የሚታደሙ ሆድ አደሮችና ተስፈኞች ናቸው:: ስለዚህም ምንም እንኳን ውጭ ጉዳይና ኤምባሲው የአስተሳሰብ ችግር እንዳለብኝ ብታምኑም ልትገነዘቡ የሚገባው እኔና እኔን የሚመስሉ ኢትዮጵያውያን ከምንም በላይ ሀገራችንን ስንወድ ሀገራችንንና ንፁሀን ህዝቦቿን ለውርደት፣ለመከራና ለስደት እየዳረገ ያለውን ክፉ ስርዓትን ግን ከልብ እንጠላለን:: ለዚህም ነው የወያኔ ካድሬዎችና ተለጣፊዎች በአውሮፓና በአሜሪካ እንዲሁም በሌሎች የዓለም ክፍሎች የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን ዓይን ለማየት ለጉድ የሚፈሩት:: ለዚህም ዋነኛው ምክንያት አንጃው በሀገራቸው ላይ የሚያደርሰው ክፋትና ጥፋት የአደባባይ ሚስጥር ስለሆነ ነው:: **(ይቀጥላል)** →